የኢ.ፌ.ዲ.ሪ
የሕዝብ ተወካዮች
ምክር ቤት
HOUSE OF
PEOPLES REPRESENTATIVES'
OF THE FDRE

# የስቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ውጤታማነት፣ ክፍተቶችን እና የመፍትሄ ሃሳቦች

**በኢትዮጵያ የህግ ባለሞያዎች ማህበር የተዘጋጀ**


**የጥናቱ አዘጋጆች**

*በቀለ በላይሁን (ዶ/ር)*
*ውብሸት ሽፈራው (ዶ/ር)*
*አበባው ምናየ (ዶ/ር)*




**ሰኔ 2013 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


**ማውጫ** ........ **II**

**አፅኅሮተ ቃላት** ........ **III**

**ምስጋና** ........ **IV**

**ማጠቃለያ** ........ **V**

**ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ** ........ **1**

1.1. የጥናቱ ዳራና ድህረ ታሪክ ........ 1

1.2. የመነሻ ነጥብ ........ 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 3

1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ ........ 3

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 3

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3

1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 4

1.6. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 4

**ምዕራፍ ሁለት፡** ........ **5**

**የጥናቱ አካሄድና የመረጃ ዳሰሳ ዘዴዎች** ........ **5**

2.1. የመረጃ ምንጮችና የአሰባሰብ ዘዴዎች ........ 5

2.2. ምላሽ ሰጭዎችን የማግኘት እና የመድረስ ሂደት ........ 5

2.3. የመረጃ ትንተና ዘዴ ........ 6

**ምዕራፍ ሶስት፡** ........ **7**

**መረጃ ትንተና፤ የግኝቶች ሃተታ እና ውይይት** ........ **7**

3.1. መግቢያ ........ 7

3.2. የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤቶች ........ 8

3.2.1. አዋጅ ቁጥር 621/2001 ለምን ተሻሻለ ........ 8

3.2.2. አዲሱ አዋጅ ያስመዘገባቸው ውጤቶች ........ 9

3.2.2.1. የሲቪል ማኅበራት አመዳደብ፣ የገንዘብ ድጋፍ እና የስራ እንቅስቃሴ ገደቦች ማሻሻያ ........ 10

3.2.2.2. የሲቪል ማኅበራት ቁጥር መጨመር ........ 12

3.2.2.3. ስለ ገንዘብ ድጋፍ አጠቃቀም ........ 13

3.2.2.4. የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባራት ........ 14

3.2.2.5. የኤጀንሲው የቦርዱ ስብጥር ........ 15

3.2.2.6. ፍትሕ የማግኘት መብት ........ 16

3.3. የአድሱ አዋጅ ውስንነቶች ........ 16

**ምዕራፍ አራት** ........ **18**

**የጥነቱ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች** ........ **18**

4.1. መግቢያ ........ 18

4.2. የጥናቱ ማጠቃለያ ........ 18

4.3. የመፍትሄ ሃሳቦች ........ 19

**4. ማጣቀሻ /ዋቢ ጽሁፎች** ........ **21**

**5. አባሪዎች** ........ **23**

# አፅኅሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| ChSA | የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ |
| CSOs | የሲቪል ማህበራት ድርጂቶች |
| *CSP/ሲ.ኤሰ.ፒ* | የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ |

# ምስጋና

ይህ ጥናት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ላገዙን ግለሰቦችና ተቋማት ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡ በመጀመሪያ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ይህ ጥናት እንዲጠና በማድረግ እንዲሁም በጥናቱ ሂደት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ስላደረገልን ላቅ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጥናት ቡዷን አባላት ያላሰለሰ ድጋፍ ባደረጉልንና አስፈላጊውንም መረጃ ባይሰጡን ኖሮ ይህ ጥናት በተያዘለት ግዜ ሊሳካ አይችልም ነበር፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ላይ ድጋፍ ላደረጉልን የምክር ቤት የጥናት ቡዷን አባላት በሙሉ በተለይም ዶ/ር ሄኖክ ስዩም ላሳዩት ቀና ትብብር ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ እንዲሁም ወ/ሪት አንችንአሉ ግዛው ያልተቆጠበ ትብብርና ድጋፍ በማድረግ ቃለ-መጠይቅ በማመቻቸትና አስፈላጊውን መረጃ በማቅረብ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛውን አስተዋጽዖ በማድረጋቸው ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው፡፡

ውድ ጊዜያቸው ሰውተው በነፃነት፤ ግልፅና ታማኝነት በተሞላበት ሁኔታ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተሳተፉ ግለሰቦችና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ሁሉ ከልብ የመነጭ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን፡፡ በመጨረሻም በዚህ ጥናት ሂደት አስፈላጊውን ትብብር ላደረገልን የኢትዮጵያ የህግ ባለሞያዎች ማህበር ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# ማጠቃለያ

ይህ ጥናት አ.ቁ.1113/2011 በኢትዮጵያ ውስጥ የሲቪል ማኅበራት ስራዎችን ከማሳለጥ አንፃር ያስመዘገባቸውን ውጤቶችና ያሉበትን ተግዳሮቶች፤ እንዲሁም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ አውዶች መሠረት የሲቪል ማኅበራት ያደረጉትን አስተዋፅዖም ይተነተናል፡፡ አዲሱ አዋጅ የሲቪል ማኅበራት የስራ እቅስቃሴ፣የገቢ ማስገኛ፣ እዲሁም የገንዘብ አጠቃቀም፤የማህበራት አመዳደብ ላይ ከፍተኛ ውጤቶችን አስመዝገቧል፡፡ በዚህ ጥናት በዝርዝር የተገለፁትን አዋጁ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች በማጠቃለል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ተኮር እንቅስቃሴን የሚያካሂዱ የሲቪል ማህበራት የተሻለ የሥራ እቅስቃሴን እንዲያደርጉ ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡
- በሲቪል ማኅበራት አሰራር ላይ ግልጽኝነት እና የተጠያቂነት መንፈስን በመፈጠሩ ማህበራት ለአላማቸው እና ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ፖለቲካዊ ምህዳሩን ከማሰፋት አንፃር እና የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ማናቸውንም የስራ እቅስቃሴ ያለምንም የገንዘብ ገደብ ማድረግ እንዲችሉ አድርጓል፡፡
- ከለጋሽ ድረጅቶች የሚገኘውን የገንዘብ መጠን 35 በመቶ ጭማሬ እንዲመዘገብ ረድቷል፡፡
- አዲሱን አዋጅ መሰረት በማድረግ 1400 አዳዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የመመዝገብ፣1800 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ዳግም የመመዝገብ እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የዜጎችን የመደራጀት መብትን አረጋግጧል፡፡
- ማናቸውም የሲቪል ማኅበራት በእያንዳንዱ እቅስቃሴያቸው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ተሳትፎ፤ ጾታዊና ኃይማኖታዊ እኩልነትን ባረጋገጠ መልኩ፤ እና የአረጋውያንና የአካል ጉዳተኛ ልጆች መብቶች ባማከለ ሁኔታ መስራት እዳለባቸው ያስቀምጣል፤ በመሆኑም ማህበራት የዜጎችን እኩልነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየሰሩ እንደሆነ ያስረዳል፡፡
- የፍትህ እና የሕግ አስከባሪ አገልግሎቶች ቅልጥፍናን ከማሳደግ አኳያ እንዲሁም ፍትህ የማግኘት መብትን ማለትም በህገ-መንግስት አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብት ያከበረና ለሲቪል ማህበራት አዲስ ምዕራፍን የከፈተ መሆኑን አመላክቷል፡፡
- ኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ተኮር ስራዎችን ከመስራት አኳያ አለም አቀፍ ድንጋጌዎችን ከማክበር አንፃር አዋጁ ከፍተኛ ውጤትን አስመዝግቧል፡፡
- ሲቪል ማኅበራት የድርጅት ንብረታቸውን እንዲያስተዳድሩ ስለፈቀደላቸው ንበረታቸውን በአግባቡ እዲጠቀሙም እረድቷቸዋል፡፡

የዚህ ጥናት ፅንሰ-ሀሳብ ሲቪል ማኅበራት በአዲሱ አዋጅ ያስመዘገቡትን ተጨባጭ ውጤት ላይ ያጠነጠነ ስለሆነ በተጠቃሚው ማህበረሰብ ላይ ያለውን ውጤታማነት አይዳስስም፣ ስለሆነም መሰረታዊ ለውጥ ማስመዝገቡን ለመረዳት ወቅቱን ጠብቆ ከማህበረሰቡ እይታ አንፃር ተጨማሪ ምርምር/ጥናት ያስፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራና ድህረ ታሪክ

ሲቪል ማህበራት ለሚለው ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለው የስራ ትርጓሜ አልተቀመጠለትም፡፡ የተለያዩ ጸሀፊዎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የተለያየ ትርጉምና ማብራሪያ ሲሰጡበት ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያየ አረዳድ እና ግንዛቤ እንደ ሲቪል ማህበራት ዓላማ እንዲሁም ሀሳቡን እንደሚረዳው ወይም ጥናት እንደሚያደርገው ግለሰብ ወይም ተቋም ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ በአብዛኛው ስንመለከት ሲቪል ማህበርሰብ የሚለው ሀሳብ ከዲሞክራሲያዊ ሂደት ጋር የማገናኘት እና ያለአግባብ ቃሉን የመጠቀም ዝንባሌም ይታያል (1)፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አጀማመር በሚመለከት ጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ ፍልስፍናዎች፣ የሰው ልጅ ያለፈባቸው የተለያዩ የሥልጣኔ ደረጃዎች እና የኑሮ እርከኖች ጋር የተቆራኘ ሲሆን በዋናነት ትኩረቱን ያደረገው የሰው ልጆችን ህይወት የተሻለ ማድረግ እና የዜጎችን በልማት ተጠቃሚነት ጋር በቀጥታ ይዛመዳል (2)፡፡ የምግባረ ሠናይ ድርጅቶች በይበልጥ ዕውቅና ማግኘት የጀመሩት የመንግስታቱ ድርጅት ቀጥሎም የዓለም የሠራተኞች ድርጅት ምስረታ ጋር ይያያዛል (3)፡፡ በሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የነበሩ ሁኔታዎች ማለትም ዓለም ወደ አንድ መንደርነት መምጣት፤ የባህሎች እርስ በእርስ መደበላለቅ፤ የአገራት መፍረስ እና ሕጋዊነት ማጣት፤ የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ አለመረጋጋት (4) የሲቪል ማህበራት በቁጥር እንዲበዙ፤ በሰብዓዊ ሥራዎች ላይ እንዲያግዙ፤ አገልግሎት እና የልማት ፕሮጀክቶችን፤ የሰብዓዊ መብት እና የፖሊሲ ቀረጻ ላይ እንዲያማክሩ፤ በአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች እንዲሳተፉ፤ ከመንግስት እና ከንግዱ ዘርፍ ጋር ጎን ለጎን የራሳቸውን ሚና እንደ ሦስተኛ አካል ሆነው የድርሻቸውን እንዲወጡ ምክንያት ሆኗል (5)፡፡

የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች በአንድ ሀገር ላይ የዜጎችን የልማትና የዲሞክራሲ እድገት፤ ሰብዓዊ መብቶች መከበር እንዲሁም የዜጎችን እኩልነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ታሪካዊ ዳራ በአንጻራዊነት ከባህላዊው እና ሃይማኖታዊው ተቋማት እና መረዳጃ ጋር ስናየው ዘመናዊው የሲቪል ማህበረሰብ እድገት የቅርብ ጊዜ ክስተት ሆኖ እናገኘዋለን (6፣7)፡፡ በዚህም መሰረት አንዳንድ እምነትን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች ሥራቸውን የጀመሩት እ.ኤ አ በ1927 ገደማ ሲሆን (8፣9) ነገርግን እንደዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ድርጅት ያሉ የእርዳታ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ሥራቸውን የጀመሩት እ.ኤ.አ ከ1930 ጀምሮ ነው፡፡ ሆኖም ዘመናዊ የሚባሉት የሲቪል ማህበራት የተመሰረቱት ከሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በተለይም የፍታብሔር ህግ በሥራ ላይ ከመዋሉ ጋር ተያይዞ ነው (6፣7)፡፡ ቀጥሎም በደርግ ዘመነ መንግስት በተለይ እ.ኤ.አ 1970ዎቹ እና 1980ዎቹ በአገሪቱ ተከስቶ ከነበረው ድርቅና ርሐብ ጋር በተገናኘ በርካታ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ችግሩን ለመደገፍ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል (10)፡፡ እ.ኤ.አ 1991 ጀምሮ በተደረገው መንግስታዊ ለውጥ ቁጥራቸው በዛ ያሉ የሲቪል ማህበራት እና የእርዳታ ድርጅቶች በሰብዓዊ ድጋፎች ላይ እንዲሳተፉም ተደርጓል (6፣8)፡፡ ሆኖም በ1997 ዓ.ም በተደረገው አገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ መንግስት የሲቪል ማህበረሰብ

ድርጅቶች ላይ የተለይ ትኩረት ማድረጉ ይታወሳል (9)፡፡ በመቀጠልም መንግስት 2001 ዓ.ም አሳሪ እና አሻሚ የተባለውን የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ ቁጥር 621/2001 በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል (11)፡፡ ይህ አዋጅ በባህሪው መሰረታዊ የተባሉት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን እና የመደራጀት መብት የሚገድብ፤ በተጨማሪም በሲቪል ማህበራት ነጻነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ እንደነበር ይጠቀሳል፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሶስት ዓመታት መንግስት በአገሪቱ ላይ እያደረገ ካለው የሕግ፣ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻዎች አንዱ የፍትህና የሕግ ማሻሻያ ሲሆን በዚህ መሰረት የሕግና የፍትሕ ማሻሻያ ጉባዔ በማቋቋም ወደ ሥራ የገባ ሲሆን በዚህ ጉባዔ ከተቋቋሙት ቡድኖች መካከል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ህግ ማሻሻል አንዱ ስለነበረ፤ ቡድኑ በአዋጁ ላይ ጥልቅ ዳሰሳ ካደረገ በኋላ፤ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ረቀቅ የማሻሻያ አዋጁን (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) በማዘጋጀት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 1.2. የመነሻ ነጥብ

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የስራ እቅስቃሴ ለመቆጣጠር እንዲሁም ተጠያቂነት ለማስፈን ለአንድ ሀገር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህግና የአሰራር ደንብ ያስፈልጋል(12)፡፡ የሀገራት ውሳኔ ለአብዛኛው ሲቪል ማህበረሰብ ተቀባይ እና ገዢ ህግ መሆን አለበት ምክንያቱም ማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ስራዎች የሀገራቱን ዜጎች ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ታሰትፎን ስለሚደግፍ ነው፡፡ ይህም ማለት የመንግስት ሚና የዜጎችን መልካም ፍላጎትና ደህንነት መጠበቅ እንዲሁም የህግን የበላይነት ማረጋገጥ ላይ ማተኮር ይኖርበታል (13)፡፡ ነገር ግን መንግስት በህግና ደንብ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የስራ ድርሻ ማሳወቅና መደገፍ እንዲሁም ገዳቢ የሚባሉ ህጎችን ወይም ደንቦችን በመፈተሽ የቁጥጥሩንና የድጋፍ ስራዎችን መስራት ይኖርበታል (14)፡፡

በመሆኑም በየጊዜው የሚለዋወጠውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ሀገራት የዜጎቻቸውን ፍላጎትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በየጊዜው ህጎቻቸውን እንደ አስፈላጊነቱ ይቀይራሉ ወይም ያሻሽላሉ፡፡ ነገር ግን በአዋጅ ወይም በሌሎች ህጎች ላይ የሚደረጉ ለውጦች እንደየሀገራቱ የፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም የሀገራቱን የተለያዩ ዓላማዎች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

በዚህም መሰረት ሀገራት እንደ አስፈላጊነቱ በአዋጆችና በሌሎች ህጎቻቸው ላይ ማሻሻያ ያደርጋሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሀገራችን ኢትዮጵያም የጀመረችውን የፖለቲካና ማህበራዊ ለውጦችን ተከትሎ በሁሉም የስራ ዘርፎች ቀላል የማይባሉ ማሻሻያዎች ተደረገዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሻሻል በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

አዋጅ ቁጥር 621/2001 የሲቪል ማህበራት እንቅስቃሴዎችን በገቢ መጠን በማገድ፣ የስራና የአስተዳደር ወጪዎችን በመወሰን፣ እንዲሁም ፍትህ የማግኘት መብቶችን በመገድብ በአንፃሩ ለኤጀንሲው ሰፋ ያለ የህግ ማዕቀፍ በመስጠት ከፍተኛ ክፍተት የሚታይበት አዋጅ ነበር፡፡ ይህ አሳሪ ህግ የሲቪል ማህበራት ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ እድገት የሚኖራቸውን ሚና አሳጥቷል፡፡ በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ የጀመረችውን የፖለቲካና ማህበራዊ ለውጦች እንዲሁም የዜጎችን ፍላጎት ለማሟላት የማያስችልና ጊዜውን የማይመጥን ከመሆኑም በላይ እነዚህን ህጎች ይዞ ብዙ ርቀት ለመጓዝ ማሰብ

አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ የማይቻል ነገር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በፖለቲካው "ተሃድሶ" ምክንያት የህዝብን ንቃተ ህሊና ለማሻሻል ጊዜውን እና የዜጎችን ፍላጎት የሚያሟላ እንዲሁም ረጅም ርቀት ለመጓዝ የሚያስችል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለህብረተሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ ለማሳካት እና የሚያከናውኑትን ተግባር በተጠያቂነት እንዲሰሩ ለማድረግ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 55 ላይ በተቀመጠው ድንጋጌ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በተሰጠው ስልጣን መሰረት በ2011 ዓ.ም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) በስራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡ የተሻሻለው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ተሻሽሎ ከወጣ ሁለት ዓመታትን ቢያስቆጥርም ከውጤታማነት አኳያ በመፈተሽና ተግዳሮቶቹንም/ያጋጠሙ ችግሮች ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ ሃሳቦችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ አሁን በስራ ላይ ያለው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ለመሻሻል ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች እንዲሁም የአዋጁ መሻሻል ያስገኛል ተብሎ ከሚጠበቀው ለውጥ አንጻር በመዳሰስ ውጤታማነቱን መፈተሽና ችግሮቹንም በመለየት ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- አዲሱ አዋጅ በሥራ ላይ መዋሉ በሲቪል ማኅበራት የስራ እቅስቃሴ፣ የገቢ ማስገኛና የገንዘብ አጠቃቀም እና የማህበራት አመዳደብ ላይ የተመቻቸ ምህዳር መፈጠሩን መለየት፤
- አዋጁ በሥራ ላይ በመተግበሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተግባራቸውን በህጉ መሰረት በግፅኝነትና በተጠያቂነት መንፈስ እየሰሩ መሆኑን መገምገም፤
- አዲሱ አዋጁ ቀድሞ ከነበረው አዋጅ ጋር ሲነጻጸር ይዞት የመጣው መልካም አጋጣሚ እና ተግዳሮቶቹን መገምገም፤
- አዋጁ ያሉበትን ውስንነቶች መለየትና ምክረ ሀሳብ መስጠት፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ሲቪል ማኅበራት ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ለውጦችን ለማምጣት እንዲሁም የዜጎችን ተሳትፎ ለመጨመር እና የዜጎችን ሰበዓዊ መብቶች ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይሁንና የዘርፉን ተሳትፎ ለማሻሻል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ተሻሻሎ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በመሆንም አዲሱ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለ ጀምሮ ያስመዘገባቸውን ውጤቶችና ያጋጠሙትን ውስንነቶች ከማየት አንፃር ጥናቶች ያስፈልጋሉ፡፡ ከምንም በላይ ጥናት መደረጉ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዙሪያ አዋጁ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች እና ያሉበትን ውስንነቶች

በአግባቡ በመለየትና ለወደፊቱ መወሰድ ያለበትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች ያመላክታል፡፡ እንዲሁም የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተሻሽሎ በስራ ላይ እንዲውል ያደረገውን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ያሉበትን ውስንነቶች ለማስተካከል የሚያስችል ምክረ-ሃሳብ በመጠቀም ዘርፉን ለማጠናከር ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በጉዳዩ ላይ ወደፊት ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አካላት እንደ መረጃ/ ግብዓትነት ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ያስመዘገባቸውን ውጤቶችና ያሉበትን ውስንነቶች ለመለየት ምክር ቤቱ በሁለት ዋና ዋና መንገዶች መመልከት ይችላል፡፡ አንዱ በሲቪል ማኅበራት የስራ እቅስቃሴ፣ የገቢ ማስገኛ፣ እንዲሁም የገንዘብ አጠቃቀም የማህበራት አመዳደብ ላይ ያስገኘውን ውጤት እና ያሉበትን ውስንነቶች በመለየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዋጁ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የስራ እቅስቃሴ ከሚጠቀሙ ማህበረሰቦች (ከተጠቃሚ) አንፃር ያስመዘገባቸውን ውጤቶችና ያሉበትን ውስንነቶች ይሆናል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በመጀመርያ የተጠቀሰው ሲሆን ማለትም በሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች የስራ እቅስቃሴ፣ የገቢ ማስገኛ፣ እንዲሁም የገንዘብ አጠቃቀምእና የማህበራት አመዳደብ ላይ ያስገኘውን ውጤትና ያሉበትን ውስንነቶች የሚዳስስ ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተዘጋጀ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ስለ ጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ እና ድህረ ታሪክ ያትታል፤ ምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ዘዴ እና የመረጃ አሰባሰብ ስልትን ያመለክታል፡፡ ምዕራፍ ሶስት በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የስራ እቅስቃሴ፣ የገቢ ማስገኛ፣ የገንዘብ አጠቃቀም፣ እዲሁም የማህበራት አመዳደብ ላይ የተመዘገቡ ውጤቶችንና ያሉበትን ውስንነቶች የሚያመላክት ሲሆን፤ ምዕራፍ አራት በአዋጁ ዙሪያ የተገኙ የጥናቱ ውጤቶች ማጠቃለያና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚተነትን ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡

# የጥናቱ አካሄድና የመረጃ ዳሰሳ ዘዴዎች

## 2.1. የመረጃ ምንጮችና የአሰባሰብ ዘዴዎች

አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ውጤታማነት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሃሳቦችን ለመተንተን ዋና ዋና መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመጀመሪያውን መረጃ ለመሰብሰብ በከፊል የተዋቀሩ ቃለ መጠይቆችን በመጠቀም ከፊል መዋቅራዊ ጥያቄዎችን፣ የተመዘገቡ ውጤቶችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በእውቀትና በውይይት በማዋሃድ የመጀመሪያውን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ጥልቀት ያላቸውን ቃለ ምልልሶች ለመደጎምና ስለ ጉዳዩ የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት ተገቢ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ደግሞ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ከተለያዩ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ ሰነዶች፣ መመሪያዎች፣ ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ ሌሎች የምርምር መረጃዎች፣ በተጨማሪም ሌሎች መረጃዎችን ከበይነ መረብ ተሰብስበዋል፡፡ ስለሆነም ሁሉም የመረጃ ምንጮች ተገቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 2.2. ምላሽ ሰጭዎችን የማግኘት እና የመድረስ ሂደት

የዚህ ምርምር ዓላማን ለማግኘት የአዲሱን አዋጅ (ቁጥር 1113/2011) ተገቢዎቹን ተዋናዮች ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ተዋናዮች ለመለየት እና ለማግኘት እንዲሁም ቃለ መጠይቅ ለማካሄድና ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ አንደኛ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የተለያዩ ጽሑፎች በማንበብ እና በዋናነት የተጠቀሱትን የአካል እና ሌሎች ተገቢ የሆኑ ተዋንያንን መለየት፤ ሁለተኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ክልል በላይ ለመስራት የተመዘገቡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ዝርዝር መፈለግ፡፡ ዝርዝሩ ከተገኘ በኋላ በአገሪቱ ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በዝርዝር መመዝገብ እና መስሪያ ቤታቸውን በአዲስ አበባ ውስጥ አድርገው የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በመለየትና ለጥናቱ ተሳታፊ የሚሆኑትን የዘፈቀደ ናሙና ዘዴን በመጠቀም መለየት፡፡ በዚህ መሠረት 18 የሲቪል ማህበራትና ሁለት የመንግስት ድርጅቶች የተሳተፉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ሰባት አዲስና 11 ነባር የሲቪል ማህበራት ተካተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሶስቱ አለም አቀፍ፣ አንድ የሙያ ማህበር እና 14 የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ተካተዋል፡፡ በሚሰሩት የስራ ዘርፍ ስናያቸው በተለያዩ የልማት ስራዎች (በትምህርት፣ በጤና፣ በእርሻ፣ በአካባቢ ጥበቃ)፣ የሰብአዊ መብቶችን ግንዛቤ በማስፋፋት፣ በአድቮኬሲ በጥናትና ምርምር፣ በሲቪክ እና ምርጫ ትምህርት ዙሪያ፣ ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን እና አረጋዊያን በመደገፉ ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡ ተጨማሪ ቃለ-መጠይቆች ከሲቪል ማህበረሰብ ኤጀንሲ እና ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ባለስልጣን ጋር በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ አዋጁ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሃሳቦች በተመለከተ መጠይቆች ተካሂደዋል፡፡

## 2.3. የመረጃ ትንተና ዘዴ

መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ መልስ ሰጪዎች የበለጠ ምቾት እንዲኖራቸው ለማድረግ ቃለ መጠይቆችን በቀላልና በግለፅ አማርኛ ተካሂደዋል፡፡ ተመዝግበው ከሚገኙት ቃለ-መጠይቆች ተመሳሳይ ምላሽ ከሰጡ ምላሽ ሰጪዎች ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ለመጻፍ ተሞክሯል፡፡ በተጨማሪም የሁለቱን የሲቪል ማህበረሰብ አዋጆች በመጠቀም በኢትዮጵያ ውስጥ ሲተገበሩ የነበሩ የጽሑፍ ትንታኔ ለማሳወቅ የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ከሁለቱም ምንጮች የተገኘው መረጃ ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች የተሰበሰቡ ሲሆን በአካባቢያዊ ደረጃ ላይ በተመሠረተ በጥራትና ገላጭ በሆነ ሁኔታ ተተንትኗል፡፡ ለዚህም ሁለቱን አዋጆች ለማነፃፀር የማጣቀሻ ነጥቦች የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ሁለቱ አዋጆች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት ይገለፅ እና ይተገበር እንደነበረ እንዲሁም አዲሱ የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ ከተተገበረ በኋላ ያስመዘገባቸው ውጤቶች፣ ያጋጠሙት ቸግሮች እና የመፍትሔ ሃሳቦች ተተንትነዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፡
## መረጃ ትንተና፤ የግኝቶች ሃተታ እና ውይይት

### 3.1. መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች አዋጅና ስራዎቻቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የስራ ተዛምዶ እንዲሁም እውቀቱና ልምዱ ካላቸው ተሳታፊዎች በቃለ-መጠይቅ እና በተለያዩ ዘዴዎች አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎችን እንዲሁም የሌሎች ጥናቶችን መዛግብት ትንተና እና ምልከታን በመጠቀም የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በአግባቡ በማደራጀት የቀረበ ትንተና ግኝቶች ሀተታ ነው፡፡

የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የአንድን ሀገር ዲሞክራሲያዊ እና ፖለቲካዊ ባህልን ከማበልፀግ አኳያ ጉልህ ሚና አላቸው(17)፡፡ ስለሆነም የሀገራትን ሰፊ ግብ ለማሳካት የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የአሰራር ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ለማስፈን የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ነው(18)፡፡ በ2001 ዓ.ም የሲቪል ማህበራት አዋጅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተለያዩ ድርጅቶች ወይም ተቋማት በተለያዮ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ይሰሩ ነበር፡፡ ቢሆንም የሲቪል ማህበራት አዋጅ ቁጥር *621/2001* እና *1113/2011* በተለየ መንገድ ስለ ሲቪል ማህበራት ግንዛቤ በመፈጠር ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር *621/2001* በርካታ ለውጦችን ቢያስመዘግብም መሰረታዊ የሆኑ ከፍተቶች ነበሩበት፡፡ በዚህም ምክንያት የነበሩትን ክፍተቶች ለመሙላት አዋጁን በማሻሻል እና የተሻሻለው አዋጅ ስራ ላይ እንዲውል ተደረጓል፡፡ በዚህ የዳሰሳ ጥናት ተሻሻሎ በስራ ላይ የዋለው የሲቪል ማህበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011*(ከዚህ በኋላ አ.ቁ 1113/2011 ይባላል)* ያስመዘገባቸውን ውጤቶች በተጨባጭ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመተንተን እና በማገናዘብ ይገመገማል እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 *(ከዚህ በኋላ አ.ቁ 621/2001 ይባላል)* ጋር በማነፃፀር ይተነተናል፡፡

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የሚታየው የሲቪል ማህበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ስራ ላይ ከዋል በኋላ በሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች የስራ እንቅስቃሴ፣ የገቢ ማስገኛ፣ የገንዘብ አጠቃቀም፣ የማህበራት አመዳደብ ላይ የተመዘገቡ ውጤቶችን እና የሚታዩ ክፍተቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን ምክር ሀሳቦች የሚቀርቡበት ነው፡፡ ይሁንና መጀመሪያ ጥናቱ አ.ቁ 621/2001 የነበሩበትን ክፍተቶች ገዳቢ ተፈጥሮን እና በሲቪል ማኅበራት ላይ በተለይም በሰብዓዊ መብቶች ላይ የተመሰረቱ ሥራዎችን በሚያከናውኑ የሲቪል ማህበራት ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ይተነትናል፤ እንዲሁም አዲሱ አዋጅ ያስመዘገባቸውን ለውጦች በተሰበሰቡት መረጃዎች የግኝት ሃተታና ያሉበትን ውስንነቶች ማቅርብ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 3.2. የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤቶች

### 3.2.1. አዋጅ ቁጥር 621/2001 ለምን ተሻሻለ

በዚህ ጥናት ከላይ እንደተገለፀው የተሰበሰበው መረጃ በአገሪቱ ውስጥ ያለው የ2018 የፖለቲካ "ሪፎርም" እና *አ.ቁ 621/2001* የነበሩበት ውስንነቶች አዲሱን *አ.ቁ 1113/2011* ለማሻሻል አስገዳጅ ሆኗል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የተጀመሩት አነስተኛ ተቃውሞዎች ወደ ሀገሪቱ ባለው በርካታ ኢ-ፍትሃዊነቶች እና ልዩነቶችን በመቃወም ወደ ትልቅ ብሔራዊ ጩኸት ወይም ተቃውሞ ተሸጋገረ፡፡ በዚህም መሰረት በ"ተሃድሶው" ምክንያት አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ወደ ስልጣን ሲመጡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሲቪል እና የፖለቲካ ምህዳሩን እንደሚያሰፉ ቃል ገብተው ነበር (19)፡፡ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን አዋጅ ከማሻሻል ጎን ለጎን ሌሎች ደንቦችን ለምሳሌ እ.ኤ.አ የ2008 የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጅ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ፣ እና እ.ኤ.አ.የ2009 የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥም እየጠበበ የመጣውን የዜግነት ቦታ መገለጫዎች ተደርገው ይወሰዱ ስለነበር ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል(16)፡፡

ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል አንደኛው የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ (ተሳታፊ[1]፡ የግል ቃለመጠይቅ) እንዳብራሩት የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ለማጎልበት፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማስቀጠልና የዜጎችን ሰበአዊ መብት ለማስከበር እነዚህ ህጎች ተሻሽለው ስራ ላይ መዋል አለባቸው የሚል ግንዛቤ ነበር፡፡ እንደ ተሳታፊው ገለፃ የመጀመሪያ *አ.ቁ 621/2001* ሲነሳ አራት ዋና ዋና ችግሮች በተደጋጋሚ ይጠቀሳሉ ያሉ ሲሆን እነሱም፡-

[1] አዋጁ ያስቀመጠው የገንዘብ ገቢ ገደብ ("10/90" ተብሎም የሚጠራው)፡-
አዋጁ በዋናነት ማሻሻያ ከሚስፈልጉት ነጥቦች አንዱና ዋነኛ ሆኖ የሚነሳው ማህበራት የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ገደብ ሲሆን ይህም "10/90" በመባል ይታወቀል(11)፡፡ በዚህ መሰረት የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን በዜግነት እና በገንዘብ ምንጭ በማገድ በሦስት ዓይነት ክፍሎች ይከፈላቸዋል(11)፡፡ በኢትዮጵያውያን የተቋቋሙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከአለም አቀፍ ምንጮች ከ10% በታች ባነሰ የገንዘብ ድጋፍ ከተቋቋሙ የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ወይም ማህበረሰብ ተብለው እንዲጠሩ፤ በኢትዮጵያውያን ወይም በኢትዮጵያ በሚኖሩ የሌሎች አገራት ዜጎች የተቋቋሙ የሲቪል ማህበራት ከአለም አቀፍ ምንጮች ከ10% በላይ የገንዘብ ድጋፍ ከተቋቋሙ የኢትዮጵያ ነዋሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበረሰቦች ተብለው እንዲሰየሙ፤ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ የተቋቋመ የሲቪል ማህበራት ነገር ግን በኢትዮጵያ የተመዘገበ ከሆነ የውጭ ዜጎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተብለው እንዲጠሩ ይደነግጋል(15)፡፡ በዚህ ክፍፍል መሰረት የሲቪል ማህበራት ስራዎችን በህግ በማሰርና በመገደብ የሚሰሯቸውን ስራዎች ውስን በማድርግ ለሀገር እድገትና ለማህበረስብ ለውጥ ይሰጡ የነበረውን ጉልሕ ሚና ገድቦታል(11)፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሰብአዊ መብት ተሟጋችነት፣ የግጭት ጉዳዮች ወዘተ ላይ እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸዋል(15)፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የተመዘገቡት የሲቪል ማህበራት ድርጀቶች የኢትዮጵያ ነዋሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል (11)፡፡ ሆኖም በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ አብዛኞቹ የሲቪል ማህበራት

ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች የበጀት እጥረት በማስከተሉ ምክንያት የሚንቀሳቀሱባቸውን የስራ ዘርፎች ለመቀነስ እንዲሁም ለመዝጋት ተገደዋል (16)፡፡

[2] በአሠራር እና በአስተዳደር ወጪዎች ምደባ ውስጥ ግልጽ ልዩነት አለመኖሩ ("70/30" ተብሎም የሚጠራው)፡፡ ይህ ማለት 70% የሚሆነው በጀት ለአገልግሎት አሰጣጥ ሥራ አቅርቦት እና ቀሪውን 30% በጀት ደግሞ ለአስተዳደር ወጪ እንዲመደብ ይደነግጋል(11):: በዚህ ምክንያት የኤጀንሲው ሰራተኞች በአዋጅ የተደነገጉትን መመሪያዎች በጥብቅ በመተረጎም የበለጠ አሳሪ እንዲሆን አድርገውታል(11)፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት 70/30 የሚለው ህግ ግልፅ አለመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጥ (on service delivery) ላይ ለማተኮሩ እንደችግር ያነሱ ነበር፡፡

[3] በኤ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 37 መሠረት ፍትህ የማግኘት ህገ-መንግስታዊ መብቶችን ይገድባል በመሆኑም በአዋጁ መሰረት የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራት ፈቃድ በሚሰረዝባቸው ወይም ስራ እንዲያቆሙ በሚደረጉበት ጊዜ ችግሮቻቸውን ወደ ፍትህ አካል በመውሰድ ይግባኝ የመጠየቅ መብት ሳይኖራቸው በአነፃሩ ኤጀንሲው ከተሰጡት ሰፊ ሀላፊነቶች እና ከቦርዱ ጋር በመጣመር የኤጀንሲው ቦርድ ውሳኔ የመጨረሻው የውሳኔ እርከን ስለነበር ፍትህ የማግኘት ህገ-መንግስታዊ መብትን ይገድባል(11)፡፡

[4] የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ (ChSA) ከመጠን ያለፈ ስልጣን እና ጣልቃ-ገብነት ይጠቀሳሉ፡፡

በተጨማሪም ሌላው የጥናቱ ተሳታፊ እንደገለፁት (ተሳታፊ[2]፣የግል ቃለመጠይቅ) በኢትዮጵያ ውስጥ ተለዋዋጭ የፖለቲካ ለውጥ መኖሩ፤ አዲሱ መንግስት ለውጭ የገንዘብ ምንጮች ምላሽ ለመስጠት የመረጠው መንገድ፤ ኢትዮጵያ የሰበአዊ መብቶችን ከማክበር አኳያ፤ የአለም አቀፍ ግደታዎችን ከማሟላት አንፃር አዋጅ ቢሻሻል የሚኖረው አንደምታ መሰረት በማድረግ ነበር፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ዋና ዋና ምክንያቶች ሲቪል ማህበራት ለሀገር ዲሞክራሲያዊ ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንዳይሰሩ ያገደ አዋጅ በሆኑ መንግስት የዜጎችን መብት መጠበቅ ላይ ሲያተኩር፣ የሲቪል ማህበራት ዜጎች የበለጠ መብትን እንዲጠይቁ የግንዛቤ ስራን መስራት ስለሚኖርባቸው አዋጁን ለማሻሻል ተችሏል (ተሳታፊ[1]፣የግል ቃለመጠይቅ)፡፡

### 3.2.2. አዲሱ አዋጅ ያስመዘገባቸው ውጤቶች

አዲሱ የሲቪል ማህበራት *ሊ.ቁ* 1113/2011 በሥራ ላይ የዋለው ሚያዚያ 2011 ዓ.ም ሲሆን በስራ ላይ ሁለት አመት አስቆጥሯል፡፡ ምንም እንኳን ውጤቱን ለመናገር ገና ቢሆንም፣*ሊ.ቁ 621/2001* ካስመዘገባቸው ውጤቶች ጋር በማወዳደር በማንኛውም የስራ ዘርፍ የተሰማሩ የሲቪል ማኅበራት ላይ አዲሱ አዋጅ ሊኖረው የሚችለውን ውጤት መለየት ተገቢ ነው፡፡ የሲቪል ማኅበራት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ኤጀንሲው እንደ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ካሉ በርካታ ሲቪል ማኅበራት አቋም ጋር ተደባልቆ በሀገር ውስጥ የተደረገው የገንዘብ ድጋፍ አጠቃቀምን በተመለከተ በመንግስትና ማህበራት መካከል

የበለጠ የተወሳሰበ ግንኙነት እንዳለ ያመላክታል፡፡ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ እንደሚያሳየው ሲቪል ማኅበራትም ሕጎችን በመቅረጽ እንዲሁም የኤጀንሲውን የአስተዳደር ባህሪ በመወሰን መሠረታዊ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት አ.ቁ 1113/2011 ያስመዘገባቸው ውጤቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

### 3.2.2.1. የሲቪል ማኅበራት አመዳደብ፣ የገንዘብ ድጋፍ እና የስራ እንቅስቃሴ ገደቦች ማሻሻያ

*አ.ቁ 621/2001 መሰረት ሲቪል ማኅበራት በተቋቋሙበት ቦታ፣ በገቢ ምንጭ፣ በአባላት ስብጥር እና የአባልነት የመኖሪያ ሁኔታ ላይ ተመሰርተው በሦስት ዓይነት ሲቪል ማኅበራት ተመድበው ነበር(11)፣ እነሱም(1) የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት፤ (2) የኢትዮጵያ ነዋሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት እና (3) የውጭ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ናቸው፡፡ ሆኖም የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መሻሻል፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ጾታዊና ኃይማኖታዊ እኩልነትን ማስፈን፣ የአረጋውያንና የአካል ጉዳተኛ ልጆች መብቶችን ማስከበር፣ የግጭት አፈታት ወይም እርቅ ማስፈን እንዲሁም የፍትህ እና የሕግ አስከባሪ አገልግሎቶች ቅልጥፍናን ማሳደግ በሚያካትቱ ተግባራት እንዲሳተፉ የተፈቀደላቸው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ብቻ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የተመዘገቡት የሲቪል ማህበራት ድርጀቶች የኢትዮጵያ ነዋሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል(11)፡፡ አዲሱ አዋጅ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች በገንዘብ ምንጮቻቸው ወይም በአባሎቻቸው መኖሪያ መሠረት አይመደቡም፡፡ በመሆኑም ሲቪል ማኅበራትን በሁለት ቡድን ማለትም በአገር ውስጥ እና በውጭ ብቻ ከፍሏቸዋል፡፡ በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወይም በውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋሙ ድርጅቶች የአገር ውስጥ ሲቪል ማኅበራት ይባላሉ፡፡ የውጭ ሲቪል ማኅበራት የሚባሉት በሌላ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋሙና በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሠሩ የተመዘገቡ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረተ የሲቪል ማህበራት ስራዎችን በተጠያቂነትና በግልፅነት በማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ ሆኖም የሚሰሯቸውን ስራዎች በማስፋት ለሀገር እድገትና ለማህበረሰብ ለውጥ እንዲተጉ ረድቷቸዋል፡፡*

*አ.ቁ 621/2001* አንቀጽ 2 ላይ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋሙ የሲቪል ማኅበር አባላት በሙሉ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ከኢትዮጵያ ገቢ የሚያገኙና ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያውያን የሚቆጣጠሯቸው የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ተብለው ይመደባሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ሰብዓዊ መብቶች ላይ የተመሰረቱ እንቅስቃሴዎችን፣ የግጭት አፈታት፣ የአድቮኬሲ ወ.ዘ.ተ ማከናወን የሚፈልጉ ሲቪል ማኅበራት ከውጭ ምንጮች ከ10 በመቶ በላይ ገንዘብ እንዲያገኙ አልተፈቀደላቸውም፡፡ ይህ ገዳቢ ባህሪው እና የሰብአዊ መብት ተኮር እንቅስቃሴዎችን በሚያካሂዱ የሲቪል ማህበራት የገቢ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ክፍተትን ፈጥሯል (11)፡፡ ይህም ችግር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሀገር ልማት እንቅስቃሴ ላይ በመሳተፍ የራሳቸውን ሚና እንዳይጫወቱ ከፍተኛ ክፍተት ፈጥሮ ነበር፡፡

በገንዘብ እና የስራ እንቅስቃሴ ገደቦች ምክንያት አብዛኛዎቹ የሲቪል ማኅበራት እንዲዘጉ ወይም በዓላማቸው እና እንቅስቃሴዎቻቸው የተመሰረተ ተግባሮቻቸውን በመተው እንደገና እራሳቸውን በአዲስ እንዲያደራጁ ሆነዋል *(16) ፡፡*

*እንደ ጥናት ተሳታፊው ገለፃ፡ በኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከተመዘገበ መሥራት ይቅርና ብዙዎቻችን ለመኖር አስቸጋሪ ሆኖብን ነበር፡፡ ብዙዎቻችን በኢትዮጵያዊያን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተመዝግበን ለመንግስት ጫናዎች በመሸነፍ ከመብታችን ጋር የተያያዙ ሥራዎቻችንን በይፋ ትተናል (ተሳታፊ³ ፤የግል ቃለመጠይቅ)፡፡*

ከዚህ በፊት የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በገንዘብ እጥረት/ገደብ ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ 2275 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ የተረፉት 1701 ብቻ ሲሆኑ፤ ከኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የቀጠሉት 110 ሲቪል ማኅበራት ብቻ ናቸው(25)፡፡ እነዚህም የተለያዩ የልማት ሥራዎችን የሚያከናውኑ እንዲሁም ዓላማቸውን እና እንቅስቃሴዎቻቸውን በማስተካከል የውጭ ገንዘብ ማግኘት የቻሉትን ያካትታል፡፡

አ.ቁ 1113/2011 ከኤጀንሲው ማረጋገጫ ሳይጠይቁ ሲቪል ማህበራት ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚያስችላቸውን የገንዘብ ድጋፍ 10% ደንብ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም የስራ ዘርፋቸው ላይ ማለትም በሰብአዊ መብቶች ላይ መሥራት፣ በአድቮኬሲ ወይም በሌላ አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ዓላማቸውን ለማሳካት ሁሉም ድርጅቶች ተስማሚ ናቸው ብለው በሚያስቡት በማንኛውም ህጋዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሳተፍ መብትን በግልፅ ይሰጣል፡፡ ህጉ ሁሉም ሲቪል ማህበራት ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደት እና የአባሎቻቸውን መብት እንዲያስተዋውቁ ያስቀምጣል፡፡ ይህ ለሲቪል ማኅበራት ከፍተኛ የሆነ ምቹ ሁኔታ እንደተፈጠረላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች አስረድተዋል፡፡ በጥናቱ ከተሳተፉ የሲቪል ማህበራት ውስጥ በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ 72 በመቶ የሚሆኑት ተጨማሪ ሥራዎችን በማቀድ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ተጨማሪ ገቢዎችንም እያገኙ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ አሁን ያለው የለጋሽ ድርጅቶች ቁጥር ከቀደምት አመታት ከነበሩት ጋር ሲነጻጸር በአማካኝ 35 በመቶ ጭማሬ አሳይቷል፤ ቢሆንም በሚጠበቀው ልክ አይደለም፡፡ የዚህ ዋነኛ ምክንያት ለጋሾች በግጭትና የተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱ ሀገራት ድጋፋቸውን በማዞራችው እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተጨማሪም በአለምአቀፍ እና በአገራችን በተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በአለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ውድቀት ስለተከሰተ በዚሁ አመት ለማግኘት ታቅዶ በነበረው ድጋፍ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የፈጠረ ሲሆን በቀጣይ አመታት በሚኖር የለጋሾች ድጋፍ ላይ መቀዛቀዝ ሊያሳደር ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

እንዲሁም 28 በመቶ የሚሆኑት ማህበራት የመደብ ቅያሪ ማድረጋቸውን ተናገረዋል፡፡ በዚህም የተነሳ አዋጁ የዜጎችን የመደራጀት መብት የጠበቀ መሆኑን፣ እንዲሁም ሲቪል ማህበራት በማንኛውም ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳትፍ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሻሻል፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጾታዊና ኃይማኖታዊ እኩልነትን እንዲሰፍን፣ የአረጋውያንና የአካል ጉዳተኛ ልጆች መብቶች እንዲከበር፣ ዜጎች በማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ፣ የፍትህ እና የሕግ አስከባሪ አገልግሎቶች ቅልጥፍናን ከማሳደግ አኳያ ጉልህ ሚና እዳለው የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡

በአገሪቱ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሰማራት የተመዘገበው የውጭ ድርጅቶች የገንዘብ አጠቃቀምን በተመለከተ አሁን በአዋጁ በማስታወቂያና በአሠራር ወጭዎች ላይ የሚወድቁትን ወጪዎች በግልጽ ያቀርባል(21)፡፡ ነገር ግን የገንዘቡ ምንጭ ከየት እንደመጣ ለምን አላማ እንደሚውል በግልፅ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የሀገርን

ሉዓላዊነት ከመጠበቅ አንፃርም በውጭ በሚኖሩ የውጭ ዜጎች የተቋቋሙ የውጭ ድርጅቶች እና አገር በቀል ድርጅቶች በሌላ የፖለቲካ ሕግ ካልተፈቀደ በቀር የፖለቲካ ፓርቲዎችን አከራካሪነት ወይም ተጽዕኖ ማሳደር አይችሉም፡፡ እንዲሁም በመራጮች ትምህርትም ሆነ በምርጫ ምልከታ ውስጥ መሳተፍ አይችሉም፡፡ አዋጁ ስለ ሥራ ነፃነት ሲደነግግ አንቀጽ 62 (5) እንዲህ ይላል፡፡

> *በሌላ ሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር የኢትዮጵያ ዜጎች በሆኑ የውጭ ዜጎች የተቋቋሙ የውጭ ድርጅቶች እና የአገር ውስጥ ድርጅቶች በማማከር (በሎቢ) የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ መሳተፍ አይችሉም፤ በመራጮች ትምህርት ወይም በምርጫ ምልከታዎች ላይ አይሳተፉም፡፡*

የጥናቱ ተሳታፊዎች(ተሳታፊ[1]፣የግል ቃለመጠይቅ) ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰጡት ምላሽ፡ የአገርን ሉአላዊነት ከማስከበር አኳያ በአዲሱ አዋጅ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት አካል ካልተፈቀደላቸው በስተቀር ወይም ከኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ጋር በአጋርነት ካልሠሩ በስተቀር ብሔራዊ ምርጫን እንዲያስተባብሩ ወይም እንዲታዘቡ እንደማይፈቀድላቸው አስረድተዋል፡፡ እንደ ተሳታፊዎቹ ገለፃ ይህ ገደብ እንኳን በቂ አለመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ በመጀመሪያው *ኢ.ቁ 621/2001* የገንዘብ ድጋፍ መገደብ ለመተቸት አንደኛው ምክንያት እንደሆነ ተናግረው፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ ሲቪል ማኅበራት በገንዘብ እጥረት ነፃ ስላልሆኑ *ኢ.ቁ* 1113/2011 በተጠቀሰው መሠረት የውጭና የሀገር ውስጥ ሲቪል ማኅበራት በጋራ በመተባበር መስራት ይችላሉ፡፡ ሆኖም የአገር ውስጥ ሲቪል ማኅበራት የመደራደር አቅም ስለሌላቸው የአገሪቱን ሉዓላዊነት አያረጋግጥም ስለሆነም የአንድ ሀገር ሉዓላዊነት በህግ መከበር አለበት ብለው ይከራከራሉ፡፡ ይህንን የመከራከሪያ ነጥብ ሌሎች ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶችም ይደግፋታል(22)፡፡ ከዚህ አንፃር ከላይ የቀረበው ተጨባጭ መረጃ ሲቪል ማህበራት በሀገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ እንደ ገለልተኛ አካል ባለመቁጠር በአገሪቱ የልማት ጥረቶች ውስጥ ነፃና አስፈላጊ ተዋናዮች እንዲሆኑ የሚያስተካክል ነው፡፡ አንዳንድ ተሳታፊዎች በዚህ ሀሳብ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል፡ እንዳነሱትም ለአንድ ሀገር ዲሞክራሲያዊ ግንባታ ሂደት ክፍትና ነፃ የሆነ ሲቪል ማህበራት ነፃነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ዓለም አቀፋዊ ስለሆነ እና ማንኛውም ዓይነት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በምርጫ ወቅትም ይሁን በሌላ አጋጣሚ መከሰታቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ ሆኖም ይህ የህግ ማዕቀፍ በዚህ ዙሪያ የሚሰሩትን የሲቪል ማኅበራት መሰናክል በመፍጠር የሲቪል ማኅበራትን ለመዝጋት የታለመ እንዳይሆን በማለት ስጋታቸውን ገልፀዋል (ተሳታፊ[4]፣የግል ቃለ መጠይቅ)፡፡

#### 3.2.2.2. የሲቪል ማኅበራት ቁጥር መጨመር

አ.ቁ 621//2001 ሁሉም የሲቪል ማኅበራት የሚጠበቅባቸውን መስፈርት አሟልተው ሲመጡ በኤጀንሲው እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡ እንደ ጥናት ተሳታፊው ገለፃ (ተሳታፍ[1]፡ የግል ቃለ መጠይቅ) በምዝገባ ወቅት አንዱና ዋነኛው መስፈርት በሚሳተፉበት የስራ ዘርፍ የስራ ፕሮፖዛል ማቅረብ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ሆኖም ይህን ማድርግ ለጀማሪ ማህበራት አዳጋች በመሆኑ ለምዝገባ ከፍተኛ እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡ በመሆኑም ለምዝገባ የሚጠይቀው መስፈርት ድርጅቶችን ለስራ የማያነሳሳ እና ከባድ ነበር፡፡ የተሻሻለው አዋጅ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ምንም ዓይነት ገደብ ሳይደረግባቸው ለዓላማዎቻቸው በመረጡት የስራ ዘርፍ በመመዝገብ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ስለሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ

የሚንቀሳቀሱባቸው የስራ ዘርፎች የሀገሪቱን የወደፊት ሁለንተናዊ የዕድገት ዕድሎች የሚያሳልጡ በመሆናቸው (የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ እና የሕግ የበላይነት ልዕልና...)፤ ኤጀንሲው ጋር ያለው የስራ መነቃቃት እና ማበረታቻ ምቹ በመሆኑ፤ የምዝገባ መስፈርቶቹም ለማሟለት ቀላል በመሆናቸው በቀላሉ ለመመዝገብ ተችሏል፡፡

አ.ቁ 1113//2011 ስራ ላይ በመዋሉ ምክንያት የሲቪል ማኅበራት ቁጥር መጨመሩን ያሳያል፡፡ በአዲሱ አዋጅ የሲቪል ማኅበራት ሕጉ ከወጣ በኋላ በአንድ ዓመት ውስጥ ነባሮች እንደገና መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል(21)፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ከኤጀንሲው በተሰበሰበው መረጃ መሠረት በክልል የተመዘገቡትን ሳይጨምር 3200 የሲቪል ማኅበራት የተመዘገቡ ሲሆን በአማካይ 1800 ነባር እና 1400 አዲስ የሚሆኑ የሲቪል ማኅበራት ተመዝገበዋል፡፡ እንድሁም በዓመት በአማካኝ 700 የሚሆኑ ማህበራትን ለመመዝገብ ተችሏል፡፡ ቃለ-መጠይቅ ካደረጉት አስራ ስምንት ሲቪል ማኅበራት ውስጥ በአብዛኛው (83.3%) እንደገና ተመዝግበዋል፡፡ ሌሎቹን ሶስት ሲቪል ማኅበራት ለምን እንደገና እንዳልተመዘገቡ በተጠየቁት መሰረት እንደገና ለመመዝገብ አዲስ ስለሆኑና የመመዝገቢያ ግዜ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ እንደተሳታፊዎቹ አገላለፅ ከዚህ በፊት ከነበረው አዋጅ በተለየ መልኩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ተኮር እንዲሁም ለሀገር እድገት ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎችን ለሚያካሂዱ የሲቪል ማኅበራት አዲስ ተስፋን የሰነቀ ይመስላል፡፡ እንዲሁም አዲሱ አዋጅ የዜጎችን የመደራጀት መብትን ያከበረ ስለመሆኑ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡

#### 3.2.2.3. ስለ ገንዘብ ድጋፍ አጠቃቀም

*በአ.ቁ621/2001* ውስጥ በሥራ እና በአስተዳደራዊ ወጪዎች ላይ የተጣለው እገዳ በስራ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፈተኛ ጉዳትን አስከትሎ ነበር፡፡ ሆኖም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ (ChSA) ባለሥልጣናት ይህንን መስፈርት ብዙውን ጊዜ ላልተገባ አሰራር ይጠቀሙበት ነበር (11)፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚያስረዱት ለChSA ከተሰጡት ሰፊ ኃላፊነቶች ጋር በመደባለቅ የምርመራ መዝገቦችን እና የፍቃድ እገዳን ያጠቃልላል፡፡ ይህ አዋጅ ለአፈፃፀም ከፍት ስለሆነ በመስመር ላይ አይደሉም የተባሉትን ሲቪል ማህበራት ለማዋከብ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው በሚል በሲቪል ማኅበራት በኩል ከፍተኛ ጥያቄና ቅሬታን አስነስቶ ነበር፡፡

አንድ የጥናቱ ተሳታፊ አክሎ እንዲህ ብሏል፡ ሌላው ችግር በሲቪል ማህበራት እና በኤጀንሲው መካከል የነበረው ግንኙነት ነበር፡፡ ኤጀንሲው ከመደገፍ ይልቅ ኤጀንሲው ወደ ሲቪል ማህበራት ቁጥጥር እና ማስፈራራት ይበልጥ ያዘነብላል ብሏል፡፡ በኤጀንሲው ያሉ ባለሥልጣናት የ70/30 (የአስተዳደርና የፕሮግራም ወጪዎች) ደንብ ምን እንደሚይዙ ግልፅ ያልሆነ የመመሪያ ክፍተቶች ተጠቅመዋል ምክንያቱም የፕሮግራም እና የአስተዳደር ወጭዎችን በግልፅ የመመደብ መንገድ በቀደመው አዋጅ ችላ ተብሎ ስለነበር፡፡

ከላይ ያለው ተጨባጭ ማስረጃ እንደሚያመለክተው የሲቪል ማኅበራት የጋራ መግባባትን ማስተካከል እንዲሁም እንደገና ማጠናከር አስፈላጊ ስለመሆኑ የቻንሆኬን ጥናት የስረዳናል (23)፡፡ እንደ መጀመሪያው አዋጅ ክፍተቶች እና ገዳቢ ተፈጥሮ፣ ገንዘብ እና እንቅስቃሴን ከመጠን በላይ የመገደብ ኃይል፣ የሥራ ማስኬጃ እና የአስተዳደር ወጪን ግልፅ አለማድረግ የመጀመሪያውን አዋጅ እንደገና የመገምገም አስፈላጊነት እና በሀገሪቷ ያለው የፖለቲካ ተሀድሶ የሲቪል ማኅበራት እቅስቃሴዎችን ቀላል ከማድረጉ በተጨማሪ አዲስ እይታን አመላክቷል፡፡

*አ.ቁ 1113/2011* የአስተዳደር ወጪን 10 በመቶ በመቀነስ የሲቪል ማኅበራት 80 በመቶ በጀታቸውን ለሥራ ማስኬጃ ወጪዎች፣ የቀረውን 20 በመቶ ደግሞ ለአስተዳደር ሥራዎች (21) መመደብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሁለቱም አዋጆች የኤጀንሲው ስልጣን አንዱ ከአዋጆቹ ጋር የሚስማማ መመሪያዎችን ማዘጋጀትና መተግበር ነው፡፡ ስለሆነም ኤጀንሲው በሕግ የተደነገገው መመሪያ ቁጥር 2/2003፤ አንድ የጥናቱ ተሳታፊ እንዳብራሩት፡ በኤጀንሲው ያሉ ባለሥልጣናት የ70/30 በግልጽ አለመቀመጡን እንደክፍተት ተጠቅመውበታል፡፡ ሁሉም ወጪዎች አስተዳደራዊ እንደሆኑ ተደርገው ነበር (ተሳታፊ[1]፡ የግል ቃለ መጠይቅ)፡፡ ነገር ግን እንደ ቁጥጥር እና ግምገማ ያሉ ወጪዎች በአዲሱ አዋጅ አስተዳደራዊ ወጪዎች አይደሉም፡፡ በአዲሱ አዋጅ ማንኛውም ለስራ የተመደበ በጀት በአግባቡና በተገቢው ቦታ እንዲሁም ግልፅነት በማስፍን ማናቸውም ሲቪል ማኅበራት ምክንያታዊ እቅድን በማውጣት ወጪንም በማብራራት ስራቸውን ይሰራሉ፡፡ ኤጀንሲውም እንዲህ ያሉ አሰራሮችን ለመከታተል የተለያዩ መመሪያዎችን በማውጣትና የግምገማና የክትትል ቡድኖችን አዋቅሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ኤጀንሲው ይህንን ውሳኔ የወሰደበት ምክንያት አንዳንድ ሲቪል ማኅበራት የክትትልና የግምገማ ወጪን ብቻ በማብራራት ሌሎች ያልተገለጹ ወጪዎችን አላግባብ በመጠቀማቸው ነው፡፡

#### 3.2.2.4. የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባራት

*አ.ቁ 621/2001* ላይ ከተሰነዘሩ ነቀፌታዎች አንዱ የኤጀንሲውን ስልጣንና ተግባር በተመለከተ ነበር፡፡ ለዚህ ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባራት በጣም ሰፊ እና ጣልቃ-ገብነት ያላበት እንዲሁም አገልግሎቶችን በሚፈልጉበት ጊዜ ያለመስጠት የነበረው ጥብቅ የቢሮክራሲያዊ መሰናክል በጣም የማይመች መሆኑን ተችቷል (11)፡፡ የተመዘገቡ ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

**የኤጀንሲው ተግባራት፡-** ምንም እንኳን መንግሥት ለአዲሱ አዋጅ ምክንያታዊነት ካላቸው ጉዳዮች መካከል በሲቪል ማኅበራት፣ በመንግሥትና በለጋሽ ድርጅቶች መካከል የልማት አስተሳሰብ ጥረቶችን ማመጣጠን ቢሆንም የድርጅቱ የልማት ሥራ ከመንግስት ፖሊሲ ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ ይህ የዘርፉ አስተዳዳሪ የአሠራር እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፡፡ እንደ ጥናት ተሳታፊው ገለፃ (ተሳታፊ[8]፣የግል ቃለ መጠይቅ) በእያንዳንዱ አስተያየት ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ አቅርቦት ቀደም ሲል በተበታተነው ኃይል እና ሃላፊነት በአንድ ነጠላ ተቋም ውስጥ ማዕከላዊ የማድረግ እና የማተኮር ዝንባሌ አለው፡፡ ምንም እንኳን አዲሱ አዋጅ ኤጀንሲውን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ብሎ ቢጠራም የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች አሁንም ድረስ የሲቪል ማኅበራትን ምዝገባና ሪፖርት ይቆጣጠራል፡፡ አዲሱ አዋጅ በኤጀንሲው አስተዳደራዊ ግዴታዎችና አሰራሮች

ላይ የጊዜ ገደቦችን ያስቀመጠ ሲሆን ለስራ ቅልጥፍና ከፍተኛ አስተዋፆ ይኖረዋል፡፡ እንደታሳተፊዎቹ ገለፃ በአዲሱ አዋጅ ኤጀንሲው ከተቆጣጣሪነት ወደ ረዳትነት ተቀይሯል፡፡

**ንብረት የማስተዳደርና ማስወገድ፡** አ.ቁ 621//2001 እና አ.ቁ 1113/2011 በይዘት አንፃር ሲወዳደሩ ለኤጀንሲው ተመሳሳይ በሚባል ደረጃ ስልጣኖች ተሰጥተውታል፡፡ አ.ቁ 621//2001 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ንብረትን ማስወገድ የሚችሉት በኤጀንሲው በኩል ብቻ ነበር፡፡ የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲገዛ የንብረቱ ባለቤትነት በኤጀንሲው እና በሲቪል ማኅበራት ስም ይመዘገብ ነበር (15)፡፡ ነገር ግን አዲሱ አዋጅ ሲቪል ማኅበራት ንብረታቸውን እንዲያስተዳድሩ ግልፅ መብቶችን ሰጥቷል (21)፡፡ የጥናቱ ታሳተፊዎች እንዳብራሩት በቀድሞው ጊዜ ንብረት እንዴት እንደምናስተዳድር ኤጀንሲው የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጥቷል በመሆኑም በኤጀንሲው ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ መኮንኖች እኛን የሚያዩን ስህተት እንደምሰራ አድርገው ነበር፡፡ ምንም እንኳን የእኛ ዓላማዎች ለተጠቃሚዎች ድጋፍ ለመስጠት ቢሆንም ሁሉም ሲቪል ማኅበራት ጥሩ ነበሩ የሚያስብል ተግባር ባይኖርም የቀደመው አዋጅ ችግሩን አልፈታውም፡፡ ይልቁንም በኤጀንሲው ለአንዳንድ ብልሹ መኮንኖች ዕድል ከፍቷል (ተሳታፊ[6]፣የግል ቃለ መጠይቅ)፡፡ ንብረቶችን በሚያስተዳድሩበት መንገድ ሲቪል ማኅበራት ለድርጊታቸው ተጠያቂ ማድረግ አስፈላጊ ነው (18)፡፡ ሌላው ተሳታፊ እንዳስረዱት (ተሳታፊ[7]፣ የግል ቃለ መጠይቅ) የሲቪል ማኅበራት ንብረቶችን አላግባብ ጥቅም ላይ የማይውል መሆኑን ለማረጋገጥ ጥሩ የቁጥጥር ማዕቀፍ አስፈላጊ እንደሚሆን አስቀምጧል፡፡ ከሁሉም በላይ እነዚህ ንብረቶች ለተጠቃሚዎች ጥቅም መዋል አለባቸው፡፡ ሆኖም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችንና ልዩ ተንቀሳቃሽ ዕቃዎችን በመንግሥት መሥሪያ ቤት ስም መመዝገብ ከተቆጣጣሪ ዕርምጃ የዘለለና ሲቪል ማኅበራት እንደ ሕጋዊ ሰው ንብረት የማፍራትና የማስተዳደር መብት ሊኖራቸው ይገባል ሲሉ አንስተዋል፡፡

#### 3.2.2.5. የኤጀንሲው የቦርዱ ስብጥር

የመጀመሪያውን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ይህ ኤጀንሲ በመንግስት የተሾሙ ሰባት አባላትን ያቀፈ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ ደግሞ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የመጡ ናቸው(15)፡፡ በአ.ቁ 1113/2011 መሠረት ይኸው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሕጉን የማሳወቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ነገር ግን የኤጀንሲው ስም አሁን ወደ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኤጀንሲ ተቀይሯል፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት ቦርዱ አስራ አንድ አባላት ያሉት (21) ሲሆን የሚካተቱትም በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የተሰየሙ ሦስት የመንግሥት አካላት ተወካዮች፤ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የተሰየሙ ሶስት ተወካዮች፤ በሲቪል ማኅበራት አሠራር ውስጥ ዕውቀት ያለውና በብቃቱ መሠረት በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚሾም አንድ ባለሙያ፤ የሁሉም የአካል ጉዳተኛ ማህበረሰብ ተጠቃሚነትን እና ተሳትፎን የማጎልበትና የማጠናከር ልምድ እና አቅም ያላቸው ሁለት የብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበር አባላት፤ ከሴቶች እና ከወጣቶች ማህበራት በራሳቸው ጥንካሬ የተወከሉ ሁለት አባላት ናቸው(21)፡፡ ይህ የተሻሻለው የቦርድ ስብጥር የሲቪል ማህበራት በእያንዳንዱ የኤጀንሲው ውሳኔ ላይ የመሳተፍ፣ ማህበራቱ ያሉባቸውን ችግሮች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የማቅረብ እና የኤጀንሲው የማስፈፀም አቅም ከመጋራት አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

#### 3.2.2.6. ፍትሕ የማግኘት መብት

በሁለቱም አዋጆች ውስጥ በዳይሬክተሩ ዋና አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኙ ድርጅቶች ለኤጀንሲው ቦርድ ይግባኝ ማለት ይችላሉ፡፡ በአ.ቁ 621/2001 መሠረት ለቦርዱ ይግባኝ ያቀረበው ድርጅት በተላለፈው ውሳኔ ካልተደሰተ እና ድርጅቱ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት/ማህበር ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ ሆኖም ድርጅቱ የኢትዮጵያ ነዋሪ የበጎ አድራጎት ድርጅት/ማህበረሰብ ወይም የውጭ በጎ አድራጎት ድርጅት ከሆነ የቦርዱ ውሳኔ የመጨረሻ ነበር(11)፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ነዋሪ በጎ አድራጎት/ህብረተሰብ እና በውጭ በጎ አድራጎት ላይ ያለው ገደብ ህገ-መንግስታዊ (ኢ-ህገመንግስታዊ) ባህሪ ስላለው በበርካታ ምሁራን እና የህግ ባለሙያዎች ትችት ይቀርብበት ነበር(11)፡፡ ይህ ድንጋጌ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37 ከተደነገገው ህገ-መንግስታዊ መብት ማለትም ፍትሕ የማግኘት መብት ጋር የሚቃረን ነበር፡፡ በመሆኑም አዲሱ አዋጅ እንዲህ ዓይነቱን ሐረግ በማሻሻል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ፈቃድ ያላግባብ ሲሰረዝ ወይም ከስራ ሲያግድ ሁሉም የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ማለትም የአገር ውስጥ ሆነ የውጭ ሲቪል ማኅበራት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት ሰጥቷቸዋል(21)፡፡ እንደ ተሳታፊው አስተያየት (ተሳታፊ[1]፤የግል ቃለ-መጠይቅ) አ.ቁ 621//2001 ጋር ሲወዳደር የይግባኝ ጥያቄዎች አ.ቁ 1113/2011 ለሰብአዊ መብት ተኮር ድርጅት እንዲሁም በህገ-መንግስት አንቀጽ 37 የተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት ያከበረና ለሲቪል ማህበራትም አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ሲሆን፤ ይህ የህግ ማሻሻያ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራትን የህግ ተጠያቂነትንና ግልፀኝነትን ከማስፈን አኳያ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደረገ ነው፡፡፡ ይህ ህግ ስራ ላይ ከዋለ ጀምሮ እስካሁን ምንም የሲቪል ማህበራት የተዘጋም ወይም ፍትህ የማግኘት ጥያቄም ያቀረበ የለም፡፡

### 3.3. የአድሱ አዋጅ ውስንነቶች

አዲሱ አዋጅ ወደ ስራ ከገባ ጀምሮ በአጭር ጊዜ በርካታ ውጤቶችን ያስመዘገበ ቢሆንም የተወሰኑ ክፍተቶች እንዳሉበትም ይህ ጥናት ያካተተ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ለ6ተኛው አገራው ምርጫ የሲቪል ማኅበራት ተሳትፎ ውስንነት፡-** መንግስት ቃል በገባው መሰረት የተጀመሩ ፖሊሲዎችና ማሻሻያዎችን በስራ ለመቀየር ወሳኝ ወቅት በመሆኑ ገዳቢ ህጎችን በማሻሻል በተለይም በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና የሰብአዊ መብት ማስከበር ረገድ ወሳኝ ሚና ለመጫወት በአዋጅ አስቀምጧል፡፡ ነገር ግን ቀደም ባሉት ህጎች ተጽዕኖ ምክንያት ሲቪል ማህበራት የመንግስት ጠላቶች ተብለው በመፈረጃቸው እንቅስቃሴያቸውን ለመገደብ ተገደው ነበር ሆኖም ብቃት ያለው ባለሙያ ለመሳብም ተቸግረዋል፡፡ ሲቪል ማኅበራት በርካታ ዕድሎች ቢኖራቸውም ነገር ግን ሁሉንም ዕድሎች የመዳሰስ እና የመጠቀም አቅም የላቸውም፡፡ ይህም ትልቁ ፈተና ሆኖ የቀረበ ሲሆን ለዚህም ማሳያ ለ6ኛው አገራዊ ምርጫ ላይ ለመስራት በርካታ የሲቪል ማህበራት ከምርጫ ቦርድ ፈቃድ ቢያገኙም ወደስራ የገቡት ግን ጥቂቶች (102) ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት ያን ያክል አመሪቂ ስራን እየሰሩ አለመሆናቸው አሳይቷል (ተሳታፊ[1]፡ የግል ቃለ መጠይቅ)፡፡

**የኤጀንሲው የአቅም ውስንነቶች፡-** አዲሱ አዋጅ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኤጀንሲ ብሎ ቢጠራም አሁንም ድረስ የሲቪል ማኅበራትን ምዝገባና ሪፖርት እንዲሁም እቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፡፡ ሆኖም አዲሱ ሕግ በኤጀንሲው አስተዳደራዊ ግዴታዎች ላይ የጊዜ ገደቦች ያስቀምጣል እንዲሁም የሲቪል ማኅበራትን መደገፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ከፍተኛ የሆነ የአቅም ውስንነት ይታይበታል፡፡ በመሆኑም የሲቪል ማኅበራትን በሚጠበቀው ደረጃ እየደገፈ አይደለም፡፡ እንዲሁም ከማህበራት ጋር አመርቂ በሆነ ደረጃ ተቀራርቦ ለመስራት ውስንነቶች አሉበት፡፡

**ረቂቅ ደንቡ አለመፅደቅ፡-** የተሻሻለውን አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ረቂቅ ደንብ ፀድቆ ለሁሉም ማህበራት የሚጠበቅባቸውን ግደታዎችና መብቶች በግልፅ ማሳወቅ ቢኖርበትም ረቂቅ ደንቡ ፀድቆ ስራ ላይ አልዋለም፡፡ ስለሆነም አዋጁ ሲሻሻል ራዕዩ ለሁሉም ሲቪል ማህበራት፣ ለመንግስት እና ለተጠቃሚዎች ፍትሃዊ የሆነ እና የተለያዩ ተፅዕኖዎች የሌሉበት ዘላቂ የቁጥጥር ማዕቀፍ እንደሆነ እና በግልፅነትና በተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ አዋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ሁሉም ተዋናዮች የተሳተፉበት ስለመሆኑ ረቂቅ ደንቡ ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቶት አለመፀደቁ አዋጁ በተገቢው ሁኔታ ስራ ላይ እንዳይውል እንቅፋት ሆኗል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የጥነቱ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 4.1. መግቢያ

የዚህ ጥናት ግብ የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተሻሽሎ በስራ ላይ እንዲውል ያደረገውን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ያስመዘገበውን ውጤት በመፈተሽና ያሉበትን ውስንነቶች በመለየት የላቀ ተግባር ማከናወን የሚያስችለውን ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ የመጨረሻ ክፍል የጥናቱን ውጤት በማጠቃለል የመፍትሄ ምክረ ሃሳቦች የሚቀርብበት ነው፡፡

### 4.2. የጥናቱ ማጠቃለያ

ከላይ በምዕራፍ ሶስት እንደተገለፀው አ.ቁ. 621/2001 ያሉበትን ክፍተቶች ስንመለከት፣ የገንዘብ ድጋፍና የእንቅስቃሴ ገደብ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብዓዊ መብት ተኮር ሥራዎችን በሚሠሩ ሲቪል ማኅበራት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በዚህ ጥናት አ.ቁ.1113/2011 ሲቪል ማኅበራት ላይ ሊኖረው የሚችለውን ውጤት በመመርመር ሲቪል ማኅበራትን በተመለከተ የተለያዩ ማዕቀፎች በማንሳት፣ የሰብአዊ መብቶችን የማረጋገጥ ሚና እና ከልማት ጋር ያላቸው ግንኙነት ፈትቷል፡፡ እዲሁም የሲቪል ማኅበራት አሰራር ላይ ግልጽነት እና የተጠያቂነት መንፈስን ፈጥሯል፡፡ በአዲሱ አዋጂ ማህበራት ለአላማቸው እና ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እዲገት፣ ፖለቲካዊ ምህዳሩን ከማስፋት አንፃር እና የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ማናቸውንም የስራ እቅስቃሴ ያለምንን የገንዘብ ገደብ ማዲረግ ይችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ተኮር ስራዎችን ለሚያካሂዱ የሲቪል ማህበራት የተሻለ የሥራ እንቅስቃሴን ለመፍጠር ተችሏል፡፡ ሲቪል ማኅበራት የድርጅት ንብረታቸውን እንዲያስተዳድሩ ስለፈቀደላቸው ንበረታቸውን በአግባቡ እዲጠቀሙም እርዲቷቸዋል፡፡ አዲሱ አዋጂ ከለጋሽ ድረጂቶች የሚገኘውን የገንዘብ መጠን 35 ከመቶ ጭማሬ አሳይቶል፡፡ በዚህም መሰረት የማህበራት ምዝገባ በከፍተኛ ሁኖታ ጭማሬ አሳይቷል ማለትም በዓመት ውስጥ በአማካይ 700 ማህበራት እዲመዘገቡ ሆኗል፡፡ የፍትህ እና የሕግ አስከባሪ አገልግሎቶች ቅልጥፍናን ከማሳደግ አኳያ እንዲሁም ፍትህ የማግኘት መብትን ማለትም በህገ-መንግስት አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብት ያከበረና ለሲቪል ማህበራት አዲስ ምዕራፍን የከፈተ መሆኑን አመላክቷል፡፡

አንድ ችግር የታዮው የኤጀንሲው የአቅም ውስንነቶች ላይ ሲሆን ስራዎችን በአግባቡና በተጠበቀው ቀንና ሰአት ለማከናውን አስቸጋሪ ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ እዲሁም የሲቪል ማኅበራት በቂ ገቢና የሰው ሀይል ማደራጀት ስላልቻሉ በርካታ ዕድሎች ቢኖራቸውም ነገር ግን ሁሉንም ዕድሎች የመዳሰስ እና የመጠቀም አቅም አላገኙም፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት ያን ያክል አመሪቂ ስራን በአገራዊ ምርጫ ላይ ተሳትፈው ለመስራት አልቻሉም፡፡ በሌላ መልኩ የተሻሻለውን አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ረቂቅ ደንብ ፀድቆ ለሁሉም ማህበራት የሚጠበቅባቸውን ግደታዎችና መብቶች በግልፅ ማሳወቅ ቢኖርበትም ረቂቅ ደንቡ ፀድቆ ስራ ላይ አልዋለም፡፡ ስለሆነም ረቂቅ ደንቡ ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቶት አለመፀደቁ አዋጁ በተገቢው ሁኔታ ስራ ላይ

እንዳይውል እንቅፋት ሆኗል፡፡ እነዚህ ውስንነቶች የሲቪል ማህበራት በተሻሻለው አዋጅ ተጠቅመው ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እዲገት፣ ፖለቲካዊ ምህዳሩን ከማስፋት አንፃር ትርጉም ያለው ሚና እናዳይኖራቸው በማድረግ ሀገሪቱ ከሲቭል ማህበራት የምታገኘውን ጥቅም አናሳ እዲሆን አድርጎታል፡፡ እነዚህን ውስንነቶች በማረም የሲቪል ማህበራት አ.ቁ 1113/2011 ሊያመጣ የሚችለውን ውጤታማነት ማሻሻል ይጠይቃል፡፡

## 4.3. የመፍትሄ ሃሳቦች

የተለያዩ የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ቅርጽን በተመለከተ ሲቪል ማኅበራት ሁል ጊዜ የውድድር ነጥብ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን የሲቪል ማኅበራት ሚና እና ትርጉም በሌሎች የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው (24)፡፡ አዲሱ አዋጅ የተለያዩ ገደቦችን ማንሳቱ ጥሩ እርምጃ ቢሆንም ያሉበትን ክፈተቶች አሻሽሎ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብ የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

መንግስት ለሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ለስራ ምቹ የሆነ ህግ በማውጣት ብቻ የዲሞክራሲ ግምባታን፣ ለኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሁም ሰበአዊ መብቶችን ማስጠበቅ አይችልም፡፡ ስለሆነም የሲቪል ማህበራት ለዓላማ ማስፈጸሚያ የሆነውን ቁልፍ ግብዓት ገቢ ከለጋሽ ድርጅቶች የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር በተለይ በሁለትዮሽ ማለትም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ጥብቅ ግንኙነት በመፍጠር የገንዘብ ግብዓት የሲቪል ማህበራት የሚያገኙበትን ስልት መቀየስ እና ለተግባራዊነቱ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ከሀገር ውስጥ ገቢ ለማሰባሰብ እንዲችሉ መንግስት መድረኩን ክፍት ማድረግ ይኖርበታል ምክንያቱም በኮቭድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ማህበራት ከውጭ ለጋሽ ድርጅቶች ማግኘት ያለባቸውን ገቢ ማግኘት ስላልቻሉ መንግስት የግሉን ዘርፍ በማስተባበር የግሉ ዘርፍ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተደራሽ እንዲሆን የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት፡፡ እንዲሁም የሲቪል ማህበራት ኤጀንሲ የሚጠበቅበትን ውጤት እንዲያስመዘግብ ያሉበትን የአቅም ውስንነቶች በመደገፍና በቂ በጀት በመመድብ በአቅምም እና በቁጥር በቂ የሆነ ሰራተኛ ለኤጀንሲው ማሟላት ይኖርበታል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲን በመከታተልና በመቆጣጠር እንዲሁም በመደገፍ የሲቪል ማህበራት የምክር ቤቱን ስራ በኢጋዥነት ማከናወን መቻላቸውን ማረጋገጥ የስፈልጋል፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የዓላማ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገቢ በማስገኘት ረገድ ያደረገው እገዛና ድጋፍ አነስተኛ ነው ነገር ግን የበለጠ ትኩረት ቢሰጥ ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ አስተዋፆ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ኤጀንሲው አዳዲስ የተቋቋሙ ድርጅቶችን በተለይም በሰበዓዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉበትን ዕድል በሲቪል ማህበራት ካውንስል አማካኝነት ቢታገዙ እንዲሁም የሲቪል ማህበራት ባደጉት ሃገራት እንደሚደረገው የራሳቸው ቋሚ ገቢ ሊያገኙ የሚችሉበትን የቢዝነስ ተቋም በጋራ እንዲመሰርቱ እገዛ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በዕቅዱ መሰርት ኤጀንሲው በየጊዜው ከሲቪል ማህበራት ጋር

በመገናኘት የጋራ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ተቀራርቦ መስራት እንዲቻል ግንባር ቀደም መሪነቱን በመያዝ ችግሮችን ለመፍታትና ሀገሪቱ ከሲቪል ማህበራት በዘለቄታዊነት ልትጠቀም የምትችልበትን ስልት ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ በተያያዘም የመንግስት አካላት የሚሰሯቸውን የልማት ስራዎች ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ኤጀንሲው ለሲቪል ማህበራት ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ሲቪል ማኅበረሰብ እና መንግሥት እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው ከሚለው አስተሳሰብ በመነሳት ይህ ግንኙነት በግልፅነትና በተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ቢሆንም የተወሰኑ የቁጥጥር ማዕቀፎች መኖር አለባቸው፡፡ ተጠያቂነት እና ግልጽነት መሰረታዊ መርሆዎች በመሆናቸው መንግስትም ሆነ ሲቪል ማህበራት ተጠያቂ መሆን አለባቸው እና ያንን ለማሳካት አዋጁን ለማስፈፀም የሚውለውን ደንብ በማፅደቅ ለሁሉም ማህበራት የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎችና መብቶች በግልፅነት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ሲቪል ማኅበራትም ከተልዕኮና ራዕዮች ጋር በሚስማማ መልኩ ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ግልፅ በሆነ አሠራር እየሠሩ መሆኑን መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ሀገርቱ ውስጥ እየተፈፀመ ያለ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ከሰብአዊ መብት ድርጅቶች የሚቀርቡላቸውን መረጃዎች፣ ሪፖርቶችን እና ምክረ ሀሳቦችን ከማጣጣል እና ከመወንጀል ይልቅ በጽሞና ተቀብለው የማስተናገድ ባህል ማዳበር ይጠበቅባቸዋል። የሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማኅበራት ገና ሙሉ በሙሉ ባለመቋቋማቸው ምክንያት ለ6ኛው አገራዊ ምርጫ ላይ ለመስራት በርካታ የሲቪል ማህበራት ከምረጫ ቦርድ ፈቃድ ቢያገኙም ወደስራ የገቡት ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የሲቪል ማኅበራት የአቅም ውስንነት ሲሆን ንቁና አቅሙ የጎለበተ ሲቪል ማኅበራትን እንደገና ማቋቋም እና ትርጉም ያለው አስተዋፆ ማድረግ እንዲችሉ መንግስት ለሲቪል ማህበራት ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በየጊዜው በመገናኘት የጋራ ምክክር በማድረግ ዘርፉን የተሳለጠ አሰራር በመተግበር የድርሻቸውን መወጣት እንዳለባቸው ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቋሚ የሆነ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በየጊዜው የውይይት ስብሰባዎችን በማድረግ ከኤጀንሲው ጋር ተቀራርቦ ለመስራት የሚጠበቅባቸው ዋና ቁልፍ ተግባር ሲሆን የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

የዚህ ጥናት ፅንሰ-ሀሳብ ሲቪል ማኅበራት በአዲሱ አዋጅ ያገኙትን ተጨባጭ ውጤት ላይ ያጠነጠነ ቢሆንም ለሚቀጥሉት ጥናቶች አስተዋፆ ያደርጋል፡፡ ሆኖም አዲሱ አዋጅ ስራ ላይ ከዋል አጭር ጊዜ በመሆኑ፤ በአለም አቀፍና በአገራችን በተከሰተው ኮቭዲ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በአለማት ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት በማድረሱ፤ በለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማስከተሉ አዲሱ አዋጅ በተጠቃሚዎች ላይ አመርቂ ውጤቶችን ላያስመዘግብ ይችላል፡፡ ስለሆነም በተጠቃሚው ማህበረስብ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማስመዝገቡን ለመረዳት ወቅቱን ጠብቆ ከማህበረሰቡ እይታ አንፃር ተጨማሪ ምርምር ያስፈልጋል፡፡

## 4. ማጣቀሻ /ዋቢ ጽሁፎች


1. Goran Hyden and Mahlet Hailemariam (2003). Voluntarism and Civil Society Ethiopia in Comparative Perspective): Source:AfricaSpectrum,Vol.38,No.2(2003),pp. 215-234, http://www.jstor.org/page/info/about/policies/terms.jsp
2. Supra note 2,P.1
3. Id.P.6
4. Yintso Gebre ; Reality Checks (2016):The State of Civil Organizations in Ethiopia, African Sociological Review Volume 202(2016) p.1
5. ibid
6. Jeffrey Clark, Civil Society, NGO s, and Development in Ethiopia: A Snapshot View (The World Bank);
7. Alelign Shibabaw (2018), The Role of Civil Society Organizations (CSO s) in Environmental Protection: The Case of MELCA Ethiopia and World Vision Ethiopia (Unpublished Masters' Thesis, Addis Ababa University, 2016) 45; International Center for Not-for-Profit Law, Ethiopia Philanthropy Law Report (ICNL 2018) 10.
8. Civic Freedom Monitor (2020): Ethiopia, available through https://www.icnl.org/resources/ civic-freedom-monitor/ethiopia (accessed 05 May 2020).
9. Wondwosen Teshome Bahiru (2009), 'Civil Society and Democratization in Africa: The Role of the Civil Society in the 2005 Election in Ethiopia' (2009) 3 International Journal of Humanities and Social Sciences 1598, 1601.
10. Kendra E Dupuy, James Ron and Aseem Prakash (2015), 'Who Survived? Ethiopia's Regulatory Crackdown on Foreign-Funded NGO s';22 Review of International Political Economy 419, 424.
11. Yeshanew, S.A. (2012) 'CSO Law in Ethiopia: Considering its Constraints and Consequences', Journal of Civil Society 8(4):369-384.
12. Claeye, F. and Van Zyl W. (2018) 'Up and down, and inside out: Where do we stand on NGO accountability?, European Association of Development Research and Training Institutes, 31:604-619.
13. Heywood, A. (2013), *Politics* (4th edition). Hampshire: Palgrave Macmillan.
14. Teshome 2018:735
15. Federal Negarit Gazeta (2009) 'Proclamation no. 621/2009' *Negarit Gazeta:* Addis Ab-aba: Birhanina Selam
16. Dupuy, K.E., and Prakash, A. (2015) 'Who Survived? Ethiopia's Regulatory Crackdown on Foreign-Funded NGOs'*, Review of International Political Economy* 22(2): 419-456
17. Roberts, T. (2019) 'Closing Civic Space and Inclusive Development in Ethiopia', *IDS Working Papers* 2019(527)

18. van Zyl and Claeyé (2018).Money, people or mission: Accountability in local and non-local NGOs: 606
19. Lakemann, T. and Soest C.v. (2019) *Ten Things to Watch in Africa in 2019*, *(GIGA Focus Afrika, 1).* Hamburg: GIGA German Institute of Global and Area Studies - Leibniz-Institut für Globale und Regionale Studien, Institut für AfrikaStudien.
20. Seckinelgin, H. (2002) 'Civil Society as a Metaphor for Western Liberalism'. *Global soci-ety*, *16*(4):357-376.
21. Federal Negarit Gazeta (2019) 'Proclamation no. 1113/2019'*, Negarit Gazeta:* Addis Ab-aba: Birhanina Selam
22. Kidan Dires Demissie (2019): The 2009 and 2019 CSO Laws in Ethiopia: From Hinderance to Facilitator of CSO Activities? The Hague, The Netherlands December 2019
23. Chandhoke, N. (2001) 'The 'Civil' And the 'Political' In Civil Society'. *Democratiza-tion*, *8*(2):1-24.
24. Chandhoke, N. (2007) 'Civil Society', Development in Practice, 17(4):607-614

## 5. አባሪዎች

**ለመጠይቅ መነሻ የሚሆኑ ነጥቦች**

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ተሻሽሎ ከወጣ ሁለት ዓመታት ያለፉት ቢሆንም ከውጤታማነት አኳያ በመፈተሸና ተግዳሮቶቹንም/ያጋጠሙ ችግሮች/ ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ ሃሳቦች ለመጠቆም የሚያስችሉ መረጃዎችን/ግብአቶችን/ ለመሰብሰብ ነው፡፡ **ይህ መጠይቅ በአገር በቀል ድርጅቶች፣ የውጭ ድርጅቶች እና የሙያ ማኅበራት አማካኝነት እንዲሞላ የተዘጋጀ ነው፡፡** መጠይቆቹ የተዘጋጁት መረጃ ሰጪዎች ለጥያቄዎቹ በነጻነት መልስ ለመስጠት እንዲያስችላቸው ክፍት በሆነ አግባብ ነው፡፡ በዚህ መጠይቅ መነሻነት የሚገኙ ግብአቶች/መረጃዎች/ ለዚሁ ጥናት አላማ ብቻ የሚወሉ ሲሆን መረጃ ሰጪዎች በፈቀዱት ልክ ብቻ መረጃዎች መስጠት ይችላሉ፡፡ ስለሆነም መጠይቁ ጥቅም ላይ የሚውለው መረጃ ሰጪዎች በፈቀዱት ልክ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን የመላሾች ማንነት እና ተቋምም በጥናቱ ውስጥ የሚጠቀሰው በተመሳሳይ መረጃ ሰጪዎቹ በፈቀዱት ልክ ብቻ ነው፡፡ በመጠይቁ የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ውጤታማነት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሃሳቦች ብሎም የድርጅቶችን አሰራር ለማሻሻል ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ በጥንቃቄና በነጻነት እንዲሞሉልን በማክበር እንጠይቃለን፡፡ ይህንን መጠይቅ ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ስለሞሉልን ከልብ እናመሰግናለን፡፡

**ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች**

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ውጤታማነት፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሃሳቦች**

**I. አንድ የግል መረጃ፡**

1.1. ጾታ፡ ____________________________________________
1.2. የትምህርት ደረጃ:____________________________________________
1.3. ኃላፊነት/የሥራ መደቡ መጠሪያ: ___________________________________
1.4. በድርጅቱ ውስጥ የኃላፊነት ደረጃ___________________________________

**II. ክፍል ሁለት ስለ የድርጅትዎ መረጃ፡**

2.1. የድርጅቱ ስም: ____________________________________________
2.2. የተቋቋመበት ዓ.ም: ______________________________________________
2.3. የቅርንጫፍ ብዛት በክልልና በስራ ዘርፍ: ___________________________
2.4. የሥራ አከባቢ (የተሰማራባቸው ዝርፎች)

| ከተሻሻለው አዋጅ በፊት | ከተሻሻለ አዋጅ በኋላ | ለለውጥ ምክንያት |
|---|---|---|
| | | |

2.5. ምድብ ( category)

| ከተሻሻለው አዋጅ በፊት (CSP/2009) | ከተሻሻለ አዋጅ በኋላ ((CSP/2019) | ለለውጥ ምክንያት |
|---|---|---|
| • *Ethiopian Charities/ Societies,*<br>• *Ethiopian Resident Charities/Societies,*<br>• *Foreign Charities* | • *Local civile society*<br>• *Foreign civile society* | |

ከላይ የተጠቀሰውን ምድብ ለመምረጥ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ በትንሹ ሶስት በጣም ወሳኝ ምክንያቶች ይግለፁልን፣ አዋጁ ከመሻሻሉ በፊት እና በኋላ በማገናዘብ፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.6. ድርጅትዎ በድጋሚ የታደሰበት ዓ.ም: ___________________________________________________

2.7. የለጋሽ ድርጅቶች/አጋሮች/ ብዛት (የውጭ)

| | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የለጋሽ /አጋር ድርጅቶች ቁጥር | | | | | | |

እባክዎን በጥያቄ ቁጥር 2.7 ውስጥ የተጠቀሰው በወቅቱ ካለው የለጋሽ /አጋር ድርጅቶች ቁጥር ውስጥ ያለውን ለውጥ ያብራሩ፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.8. ከዚህ በፊት(CSP/2009) እና ባሁን ጊዜ ወይም CSP/2019 ከተሻሻለ በኋላ ድርጅቱ የሚያገኘው እርዳታ በምን ያክል ፐርሰንት የተሻሻለ ይመስሎታል፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የተሻሻለው አዋጅ (CSP/2019) ድርጅትዎ ከለጋሽ ድርጅቶች የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ቀነሰው ወይስ ጨምሮታል? እባክዎን የታሻሻለው አዋጁ የሚያገኙትን የገንዘብ/የፈንድ መጠን ካሻሻለው ወይም ከጎዳው እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሆን ያብራሩ፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## ክፍል ሶስት ስለ ተሻሻለው የCSO ህግ መረጃ፡

**3.1.** ድርጅትዎ በተከለሰው/በተሻሻለው አዋጁ ውስጥ የተዘረዘሩትን የገንዘብ ፍላጎቶችና የምዝገባ መስፈርቶችን እንዴት እንዳሟላ በዝርዝር ያብራሩ፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የተሻሻለው አዋጅ ለድርጅትዎ ያደረገው አስተዋፆ ካለ እንዲሁም ድርጅትዎን አውኮት ከሆነ እንዴትና በምን መንገድ እንደሆነ ቢገልፁልን? እባክዎ በዝርዝር ያብራሩልን. በፕሮግራም እና በአስተዳደራዊነት አሰራር ላይ

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**3.2.** ድርጅትዎ ከ8 የተሻሻለ እና አዲስ ከተሰጠ መመሪያዎች ተጠቃሚ ሆኗል? እባክዎን ለድርጅትዎ አስተዋፅዖ ያደረገውን መመሪያ ቢገልፁልን፣ እንዲሁም በምን መንገድ እንደጠቀሞዎት ቢያብራሩት?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------

**3.3.** አዲሱ አዋጅ አጠቃላይ የድርጅቱን ክንውን እና ግብ እንዲጨምር አድርጓል? ከሆነእንዴት? የቀደሞውን አዋጅ አፈፃፀም እንዴት እንዳሳለፈ ያውቃሉ? ቢያብራሩት

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**3.4.** ቀደም ሲል በCSOs ሥራ ላይ የሚያጋጥም የቀደመው የCSO ሕግ ችግሮች ምን ነበሩ?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**3.5.** የተሻሻለው አዋጅ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ይመስልዎታል? መልሰዎ አዎ ከሆነ ለምን እንዳመኑበት ምክንያት እባክዎን ያብራሩ.

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**3.6.** በአጠቃላይ የCSOs አሰራር ውጤታማ እንዲሆን ወይም ተለውጠው ማየት የሚፈልጉትን አገልግሎቶች ለመንግስት ወይም ለCSO ኤጀንሲው የሚያስተላልፉት ምክረ ሀሳብ ካለውት ቢገልፁልን፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## ለቃለ መጠይቅ መነሻ የሚሆኑ ነጥቦች

ይህቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1113/2011) ተሻሽሎ ከወጣ ሁለት ዓመታት ያለፉት ቢሆንም ከውጤታማነት አኳያ በመፈተሽና ተግዳሮቶቹንም/ያጋጠሙ ችግሮች/ ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ ሃሳቦች ለመጠቀም የሚያስችሉ መረጃዎችን/ግብአቶችን/ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው ጥያቄዎችን ቅርጽ ለማስያዝ ሲሆን በቃለ መጠየቅ ግዜ ከነዚህ ጥያቄዎች በመነሳት ዘር ዘር ያለ ውይይት የሚደረግበት ይሆናል፡፡ መጠይቆቹ የተዘጋጁት መረጃ ሰጪዎች ለጥያቄዎቹ በነጻነት መልስ ለመስጠት እንዲያስችላቸው ክፍት በሆነ አግባብ ነው፡፡ በዚህ መጠይቅ መነሻነት የሚገኙ ግብአቶች/መረጃዎች/ ለዚሁ ጥናት አላማ ብቻ የሚውሉ ሲሆን መረጃ ሰጪዎች በፈቀዱት ልክ ብቻ መረጃዎች ይሰበሰባሉ፡፡ ስለሆነም ለቃለ መጠይቁ ጥቅም ላይ ሊወሉ መሳሪያዎች መረጃ ሰጪዎች በፈቀዱት ልክ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን የቃል ሰጪዎች ማንነት እና ተቋምም በጥናቱ ውስጥ የሚጠቀሰው በተመሳሳይ መረጃ ሰጪዎቹ በፈቀዱት ልክ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ቃለ መጠይቅ የተባሩንን አስቀድመንም እናመሰግናለን፡፡ ይህ ቃለ መጠይቅ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ለሲቪል ማህበረሰብ ኤጀንሲ ቦርዱ ሊቀመንበር እና የሲቪል ማህበረሰብ ኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር እንዲያለግል የተዘጋጀ ነው፡፡

**ትኩረት የሚደረግባው ነጥቦች**

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ውጤታማነት፣ ያጋጠሙ ቸግሮች እና የመፍትሔ ሃሳቦች**

**1. COS በኢትዮጵያ ውስጥ፡**

- ለኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለሰብአዊ መብት እና ለአገር ዲሞክራሲያዊነት በማበርከት ደረጃ ያለው አስተዋፆ ምን ይመስልዎታል?
- የCSOs አስተዋፆ ያለው አዝማሚያ( trend) እንዴት ነው? (እየጨመረ/እየቀነሰ የሚሄድ)?
- በአጠቃላይ ያለውን አስተዋፆ ማበርከት ምን ያስባሉ?,

**2. የቀደመው አዋጅ (621/2009) እና የተሻሻለው አዋጅ (CSP/2019)፡**

- የቀደመው አዋጅ (621/2009) ምን ስህተት ነበረው?
- የተሻሻለው አዋጅ በመመዝገቢያ (registration), የአገልግሎት ልዩነት (service diversity), ገቢ ከማግኘትና ከመጠቀም (income generation and utilization) አናፃር ምን ለውጥ አምጥቷል?
- ኢትዮጵያ አዲሱን ሕግ በማሻሻል ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን ከሟሟላት አንፃር ያለውን ለውጥ እንደት ያዩታል?,
- በአጠቃላይ ለውጡን እንዴት ያስተውሉታል/ይመዘኑታል?

**3. የተሻሻለው አዋጅ (CSP/2019)፡**

- በአስተዳደራዊ እና በፕሮግራም አገልግሎት ውስጥ የፈንድ አጠቃቀም ስላለው አስተዋፆ ምን ማለት ይችላሉ?
- ከቀደመው የCSP / 2009 ተፅዕኖ ጋር ሲነፃፀር አጠቃላይ አስተዋፆ እንዴት ይገልፁታል?

4. ቀደም ብለው እንደሚያውቁት አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት/ 90% የሚሆነውን ወጭ ከአገር ውስጥ መሰብሰብ በጣም ከባድ ነው ይላሉ፡፡ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት 30% የአስተዳደር ወጪ በቂ አለመሆኑን እና በአገልግሎት አሰጣጥ(on service delivery) ላይ ማተኮሩ እንደችግር ያነሱ ነበር፤ ሆኖም የተሻሻለው አዋጅ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ከመፍታት አንፃር ምን አስተዋፆ አለው? እንዴት?

5. **የተሻሻለው አዋጅ (CSP/2019)፡**

- በማህበራት ነፃነት ላይ፣ በአስተዳደራዊ አሰራር ላይ፣ በማህበረሰብ ዲሞክራሲዊ ተሳትፎ ላይ (ለጋሽ ድርጂቶች፣ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያን፤ ህጻናት፤ አደጋ ለተጋለጡ ሰዎች፤ አናሳ ማህበረሰብ) ተሳትፎ ላይ ያመጣው ለውጥ?

- በአጠቃላይ ባለው አሰራር በማህበራት ሰብአዊ መብቶችን ከመጠበቅ አንፃር ያለው አዝማሚያ እና ገለልተኝነት እንዴት ነው? ማዕቀቦችስ?

**6. የተሻሻለው አዋጅ(CSP/2019)፡**

- እንደ ሰብአዊ መብቶች፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለውጭ/ኢትዮጵያ በተወሰኑ ዘርፎች የCSOs ቁጥር ጨምሯል ወይስ ቀንሷል? ለምን?
- በሲቪል ማህበረሰብ ነፃነት (ፍላጎት ሥራ አሰራር) የተሻሻለው አዋጅ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የተዘጉ CSO ድርጂቶች ይኖራሉ? ካሉ ለምን ተዘጉ?
- የተሻሻለው አዋጅ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለውጦች አስተውለዋል? የእነዚህ ለውጦች መንስኤ ምን ይሆናል?

7. በሲቪል ማህበረሰብ ሚና ላይ ያለው ኃይል እና የሀይል ሚዛን እንዴት ያዩታል? የፍርድ ቤት ሂደቶች?

8. በCSOs አሰራር ውስጥ የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች ምንድናቸው? ኤጀንሲው ምን ዓይነት ችግሮችን ነው መቅረፍ የሚችለው?

9. በአጠቃላይ የCSO አሰራር ውጤታማ እንዲሆን ወይም የተለውጠው/የተሻሸለው ማየት የሚፈልጉትን አሰራር ለመንግስት ሊጠቁሙ ወይም የሚያስተላልፉት ምክረ ሀሳብ ካሎት ቢገልፁልን?